DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# ምልክት የማያሳዩ (Asymptomatic) ሰዎች የትምህርት ቤት የCOVID-19 ምርመራን ለማድረግ፣ ፈቃድ መስጫ ቅጽ

**የዲሲ ጤና (DC Health) እና የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፤ ልጅዎን ለCOVID-19 መበከል ምርመራ ለማድረግ፣ የእርስዎን ፍቃድ ለማግኘት** እና የተሰበሰበውን የመረጃ-ስብስብ (data) አግባብ-ካላቸው ባለስልጣናት ጋር ለማጋራት፣ ይህን ቅጽ ይጠቀማሉ። በምልክቶች፣ ምርመራ፣ እና የኮሮናቫይረስ ምላሽ ላይ፣ ተጨማሪ መረጃ በcdc.gov/coronavirus ላይ መገኘት ይችላል። የኮሮናቫይረስ ምልክቶች እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ምላሽን በተመለከተ፣ ተጨማሪ መረጃ በcoronavirus.dc.gov ላይ ማግኘት ይችላል። ደህንነቱ-የተጠበቀ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር፣ የCOVID-19 ስርጭትን በመከታተል ላይ የእኛን ታታሪነት ይጠይቃል። ይህ ምርመራ በነፃ (ምንም-ክፍያ የሌለው) እና በፍቃደኝነት የሚደርግ ነው።

**እንዴት ገብቼ መካፈል (opt in ማድረግ) እችላለሁ?** ልጅዎ ምርመራው እንዲደረግለት፣ ይህን የፍቃድ-ወረቀትን፣ ሙሉ-በሙሉ ሞልተው እና መልሰው ማስገባት አለብዎት። ይህ የፍቃድ-ወረቀት፣ በልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ይቀመጣል። በየጊዜ ልጅዎ በተመረመረ ጊዜ፣ ምርመራውን ለሚያደርገው ቡድን ይቀርባል። ይህ፣ ከወላጅ/አሳዳጊ የተሰጠ-ፍቃድ ሳይኖር፣ ልጆችን ከምርመራ ለመጠበቅ ነው። ይህ ፈቃድ-መስጫ ቅጽ፣ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ ለ**90 ቀናት** የጸና ነው።

**እንዴት አለመካፈል (opt out ማድረግ) እችላለሁ?** ልጅዎ ለCOVID-19 ምርመራን እንዲደረግለት እንደማይፈልጉ የሚገልጽ የፅሁፍ ደብዳቤ በመላክ፤ በማንኛውም ጊዜ የሰጡትን ፈቃድ-መስጫ መሻር ይችላሉ።

**ምርመራው ምንድነው?**
***ከተስማሙ፣*** ልጅዎ ለCOVID-19 ቫይረስ ነፃ የህክምና ምርመራ ያገኛሉ። **ከዚህ ጋር አባሪ ሆነው የተያያዙት ሰነዶች፣ ጥቅም ላይ ሊውል ስለሚችሉ የምርመራ ዓይነቶች ተጨማሪ መረጃን ይሰጣሉ።** ለምርመራ ናሙናዎችን ለመውሰድ ከQ-Tip® ጋር የሚመሳሰል፣ ትንሽ የመጥረጊያ መሳሪያን፣ የአፍንጫ ፊት-ለፊት በኩል፣ በሁለቱም የአፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ መክተትን ይጠይቃል። ይህ ምርመራ በዲስትሪክቱ የሕዝብ የምርመራ ጣቢያዎች ውስጥ ከሚደረገው ምርመራ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምርመራ ምክንያት፣ በCOVID-19 በሽታው የመያዝ ስጋቶች አይኖሩም።

**ስለ ምርመራው ውጤቶች እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**
የምርመራ ውጤቶቹ፣ ለእርስዎ በቀጥታ ይላካል። በሚሰጡት የኢሜል አድራሻ አማካኝነት፣ ውጤቶቹ በኢሜል ይደርስዎታል። ይህ ፈጣን (rapid) ምርምራ አይደለም። በተለምዶ፤ ውጤቱ በ5 ቀናት ውስጥ እንደሚደርስ ይጠብቁ። የምርመራ ውጤቱን በተመለከተ የ'**LabCorp Laboratory**'ን **የስልክ መደወያ ማዕከልን: በ1-800-762-4344** በመደወል ውጤቱ የደረሰበትን ሁኔታ መከታተል ይችላሉ።

**የልጄ የምርመራ ውጤቶች፣ ሲደርሰኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

- የበሽታው ቫይረስ እንዳለ (Positive) ውጤቶች: የልጅዎ የምርመራ ውጤት ቫይረሱ እንዳለ (Positive) ከሆነ፣ ልጅዎ ቫይረሱ ያለበት እና ማሰራጨት ይችላል ማለት ስለሆነ፣ የምርመራ ውጤቶችን ለመገምገም እና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ለመነጋገር፣ እባክዎ ወዲያውኑ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ-ሰጪ ያነጋግሩ። ልጅዎን ቤት ውስጥ ማቆየት አለብዎ እና ወደ ትምህርት ቤት ለማስመለስ የጤና እና የትምህርት ቤት መመሪያዎችን ይከተሉ። ልጅዎ የCOVID-19 ምርመራው ቫይረሱ እንዳለ (Positive) ከሆነ፣ ከዲሲ የጤና (DC Health) የንክኪ መከታተያ (Contract Tracers) የስልክ ጥሪ ይደርስዎታል።

- የበሽታው ቫይረስ እንደሌለ (Negative) ውጤቶች: የልጅዎ የምርመራ ውጤት ቫይረሱ እንደሌለ (Negative) ከሆነ፣ ይህ ማለት ቫይረሱ ልጅዎ ውስጥ አልታየም ማለት ነው። በበሽታ ቁጥጥር እና መከላከያ ማዕከል (Centers for Disease

Control and Prevention (CDC)፣ የሚመከሩትን፤ ንጽህናን እና የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ ልምምዶችን ይቀጥሉ። ልጅዎ ምልክቶችን ካሳየ/ች፣ የምርመራ ውጤቶቹ ምንም ሆነ ምን፣ ለልጅዎ የጤና እንክብካቤ-ሰጪ መደወል አለብዎት። ለዲስትሪክቱ ነዋሪዎች፣ የCOVID-19 ህክምና ነፃ ነው።

**የመረጃ-ስብስብ (Data) እና ሪፖርት ማድረግ**

ከዚህ ቅጽ የሚገኙ፣ የመረጃ-ስብስብ (Data) እና የምርመራው ውጤቶች እንደ COVID-19 ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች ይሰበሰባሉ እና ለሚመለከታቸው የትምህርት ቤትና የጤና ባለስልጣናት ሊጋሩ ይችላሉ። የልጅዎ የCOVID-19 ውጤቱ ቫይረሱ እንዳለ (positive) ከሆነ፣ ማንነቱ ለሌሎች ይፋ አይደረግም።

**በገጹ ጀርባ ቀጥሏል።**

| **የሚገኙበት አድራሻ** \| ተሞልቶ መጠናቀቅ ያለበት፤ በወላጅ/አሳዳጊ/ተማሪ (ዕድሜው 18 አዓመት ወይም በላይ ከሆነ) | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **የተማሪ የመጨረሻ (Last) ስም:** | **የተማሪ የመጀምሪያ (First) ስም:** | | | **ትውልድ ቀን:** | |
| **የትምህርት ቤት ስም** | | | | **ዋርድ (Ward):** | |
| **የመኖሪያ አድራሻ:** | **አፓርትማ:** | **ከተማ:** | | **ስቴት:** | **ዚፕ፡** |
| **የወላጅ/አሳዳጊ ስም:** | **ስልክ:** | | **ኢሜል፡** | | |
| **በአስቸኳይ የአደጋ-ጊዜ ተጠሪ ስም:** | | **በአስቸኳይ የአደጋ-ጊዜ ተጠሪ ስልክ:** | | | |

ከታች በመፈረም፣ ከዚህ በታች ያሉትን አረጋግጣለሁ:

- ይህንን ቅጽ ነፃ ሆኜ እና በፍቃደኝነት ፈርሜያለሁ፤ እና ከዚህ በላይ ስሙ ለተገለጸው ልጅ፣ ውሳኔዎችን ለማድረግ ሕጋዊ ሥልጣን አለኝ።
- ለCOVID-19 ብክለት፣ ልጇ እንዲመረመር ፍቃዴን ሰጥቻለሁ።
- በልጇ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኝ የሚመለከተው ኃላፊ የሰጠሁትን ፈቃድ እንደሻርኩ በፅሁፍ ካላስታወቅኩ በስተቀር፣ የሰጠሁት ፈቃድ፣ በዚህ ቅጽ ላይ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ ለ90 ቀናት የጸና ነው።
- የልጇ የምርመራ ውጤቶች እና ሌሎች መረጃዎች በሕግ በተፈቀደው መሠረት፣ ይፋ ሊደረጉ እንደሚችሉ ተረድቻለሁ።
- እድሜዬ 18 ወይም ከዚያ በላይ ወይም በሌላ ሁኔታ ለራሴ ጤንነት ፍቃድ ለመስጠት በሕግ የምችል ተማሪ ከሆንኩ፤ "የኔ ልጅ" የሚለው ማጣቀሻ፣ እኔን የሚመለከት በመሆኑ እና እራሴን ወክዬ በዚህ ቅጽ ላይ ልፈርም እችላለሁ።
- ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሰራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ፤ ለድርጊቶች ወይም ግድፈቶች፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ የታሰበበት ጥፋቶች፣ ከባድ ቸልተኝነት፣ ወይም ሆን-ተብሎ መጥፎ ምግባር ካልሆነ በስተቀር፣ ከሲቪል ተጠያቂነት ነፃ እንደሚሆኑ ተረድቼ፣ ተስማምቻለሁ።
- ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሰራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ፤ በካምፓስ ውስጥ በመማር የተነሳ፣ የተለየ ተማሪው በቫይረሱ ለመያዙ ተጠያቂ ተደርገው ሊወሰዱ እንደማይችሉ ተረድቻለሁ።

**የፈቃድ ስምምነት መስጫ፣ ፊርማ:**

| **የወላጅ/አሳዳጊ/የተማሪ (18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ) ፊርማ፡** | **ቀን፡ (ወር/ቀን/ዓም)** |
|---|---|
| | |

**OFFICE USE ONLY** | Consent form received by School Registrar and School Nurse

| የነርስ ስም: | ፊርማ: | ቀን: |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# በDCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ምልክት የማያሳዩ (Asymptomatic) ሰዎች የCOVID-19 ምርመራ: ለወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና ተማሪዎች፤ መረጃዎች

ምልክት ለማያሳዩ (Asymptomatic) ሰዎች የCOVID-19 ምርመራ፤ የሚጠቅመው ለወላጆች ስለ ልጃቸው የትምህርት ቤት አካባቢ መረጃ ለመስጠት ነው። መደበኛ-ምርመራን ማድረግ፣ ትምህርት ቤቱ በአካል ተገኝቶ (in-person) የመማር ሂደቱን ለማከናወን፤ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለወላጆች እና ተማሪዎች ሊያረጋግጥላቸው ይችላል።

- ምርመራ የሚደረገው፣ የተሞላ የስምምነት መስጫ ቅጽ ላላቸው ተማሪዎች ብቻ ነው።
- ምልክት ለማያሳዩ (Asymptomatic)፣ ምርመራ የሚደረገው በአፍንጫ ስዋብ (nasal swab) ነው። አብዛኛውን ጊዜ፣ ውጤቱ በ5 ቀናት ውስጥ ይደርሳል። ውጤቶቹ ከተማሪው የእንክብካቤ-ሰጪ ጋር ግንኙነት በማድረግ ይገለጻል።
- የልጅዎ ምርመራ ውጤቶች *ቫይረሱ እንዳለ የሚያሳይ (Positive)* ከሆነ፣ የምርመራ ውጤቶችን ለመመልከት እና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለመወያየት፤ እባክዎን ወዲያውኑ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ-ሰጪ ያነጋግሩ። ልጅዎን ቤት ውስጥ ማቆየት አለብዎ እና ወደ ትምህርት ቤት ለማስመለስ የጤና እና የትምህርት ቤት መመሪያዎችን ይከተሉ።
- የልጅዎ የምርመራ ውጤቶች *ቫይረሱ እንደሌለ (Negative)* ከሆኑ፣ ይህ ማለት ቫይረሱ በልጅዎ ናሙና ውስጥ አልታየም ማለት ነው። በበሽታ ቁጥጥር እና መከላከያ ማዕከል (Centers for Disease Control and Prevention (CDC)፣ የሚመከሩትን፤ ንጽህናን እና የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ ልምምዶችን ይቀጥሉ። ልጅዎ ምልክቶችን ካሳየ/ች፣ የምርመራ ውጤቶቹ ምንም ሆነ ምን፣ ለልጅዎ የጤና እንክብካቤ-ሰጪ መደወል አለብዎት።
- የምርመራ ውጤቶቹ እንዳስፈላጊነቱ፤ ከትምህርት ቤቱ ጋር፣ ከዲሲ ጤና (DC Health)፣ ወይም ሌሎች የአካባቢው እና የፌዴራል የሕዝብ ጤና ባለስልጣናት ጋር፤ እንደአስፈላጊነቱ ሊጋሩ ይችላሉ።
- በቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ (Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA) መሠረት፣ እና የአካባቢው ግላዊነት ጥበቃዎች መሠረት፣ ተማሪውን በግል-ሊገልጸው የሚችለውን መረጃ ለሕዝብ ይፋ አይደረግም። ሁሉም መረጃ በምስጢር ተይዞ ይቆያል።

CDC፣ ማንኛውም በCOVID-19 የተበከለ ሰው ምልክቶችን ካየ በኋላ፣ እንደ-ምልክቶቹ ክብደት መሠረት፣ ከ10 እስከ 14 ቀናት እራስን አግልሎ (quarantine) ማድረግ አለበት።

አንድ ግለሰብ በCOVID-19 ምርመራ ቫይረሱ እንዳለ (positive) ሆኖ ከተገኘ፣ ሊተገበረው ስለሚገባ መመሪያ - ተጨማሪ የሆኑ መረጃዎችን በcoronavirus.dc.gov/healthguidance ሊገኝ ይችላል።

ስለበሽታው እና የራስዎን እና የቤተሰብዎን ደህንነት እንዴት ጠብቀው መቆየት እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የCDC የኮሮናቫይረስ ድህረ-ገጽን በcdc.gov/coronavirus ይጎብኙ።

ወረርሽኙን ለመከላከል ዲስትሪክቱ እየወሰደ ያለውን እርምጃዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የDC

የኮሮናቫይረስ ድህረ-ገጽን በ coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።

ስለትምህርት ቤትዎ በCOVID-19 ምላሽ መስጫ ጥረቶችን በተመለከተ፣ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን የትምህርት ቤቱን አስተዳደር እና/ወይም የትምህርት ቤቱን የሬጅስትራር ቢሮን ያነጋግሩ።

**በገጹ ጀርባ ቀጥሏል።**

**የኮሮናቫይረስ ምልክቶች**

- የሰውነት ሙቀት 100.4 ወይም ከዚያ በላይ
- ብርድ-ብርድ ማለት
- ማሳል
- የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር
- ድካም
- የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመም
- አዲስ የሆነ ጣዕምን ወይም ሽታን-ማሽተት ማጣት
- የጉሮሮ ቁስለት
- መታፈን ወይም ከአፍንጫ ፍሳሽ መውጣት
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ
- ተቅማጥ
- በአጠቃላይ፣ ጤንነት ያለመሰማት ሁኔታ

ልጅዎ የጤና እንክብካቤ-ሰጪ ከሌለው፣ እባክዎን የ'DC Pediatric Immunization' ቦታዎችን በመጎብኘት፣ እንክብካቤ-ሰጪ ይፈልጉ። በdchealth.dc.gov/service/immunization መገኘት ይችላሉ።